# መመሪያ ቁጥር 983/2016

## ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን የተፈራረሙትን የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን በሚዋሰኑባቸው የድንበር አካባቢዎች የሚገኙ የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ከመሀል ሀገር በቀላሉ ሊያገኟቸው የማይችሏቸውን የፍጆታ እቃዎች በጠረፍ ንግድ አማካኝነት እንዲቀርቡላቸው ለማድረግ የሚያስችል የጠረፍ ንግድ ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ. ፌብሯሪ 24 ቀን 2017 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተፈራረሙ በመሆኑ፤

ተፈራራሚ ሀገራቱ የጠረፍ ንግድ ማስፈጸሚያ መመሪያ በማውጣት ፕሮቶኮሉን መተግበር እንዳለባቸው በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከተ በመሆኑ፤

በድንበር አካባቢ ህጋዊ የጠረፍ ንግድ ስርዓትን መዘርጋት በአካባቢው የሚስተዋለውን የኮንትሮባንድ እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ ለመቀነስ እና በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን ጎረቤት ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር በድንበር አካባቢ ሰላምና ፀጥታ ለማስፈን የሚረዳ መሆኑን በመገንዘብ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 35 (2) እና 52(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

<u>ክፍል 1</u>

<u>ጠቅላላ</u>

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ “የኢትዮጵያ እና የደቡብ ሱዳን የጠረፍ ንግድ መመሪያ ቁጥር983/2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>.ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **“የድንበር አካባቢ”** ማለት ኢትዮጵያ እና ደቡብ ሱዳን ከሚዋሰኑበት ድንበር ጀምሮ በዘጠና (90) ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ ያሉ ቦታዎች ናቸው፤

2/ **“የጠረፍ ነጋዴ”** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የጠረፍ ንግድ ፈቃድ የተሰጠው በድንበር አካባቢ የሚኖር የተፈጥሮ ሰው ነው፤

3/ **“የጠረፍ ንግድ ምርቶች”** ማለት በዚህ መመሪያ እንደቅደም ተከተላቸው በአባሪ-1 እና በአባሪ-2 የተዘረዘሩት የወጪ ምርቶች እና የገቢ ምርቶች ናቸው፤

4/ **“የድንበር በር”** ማለት ኢትዮጵያ ከደቡብ ሱዳን ጋር በምትዋሰንበት ድንበር የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የጉምሩክ ሥነሥርዓት አገልግሎት የሚሰጥባቸው በሮች ናቸው፤

5/ **“ሚኒስቴር”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

6/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ እና በደቡብ ሱዳን የድንበር አካባቢ በሚካሄድ የጠረፍ ንግድ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ጠረፍ ንግድ

### 4. በጠረፍ ንግድ ስራ ላይ መሰማራት ስለሚችሉ ሰዎች

በመደበኛ ንግድ ስራ ላይ ያልተሰማራ እና በድንበር አካባቢ የሚኖር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጠረፍ ንግድ ስራ ላይ መሰማራት ይችላል።

### 5. የጠረፍ ንግድ ምርቶች

1/ የጠረፍ ነጋዴ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ሱዳን ማስወጣት የሚችለው በዚህ መመሪያ አባሪ-1 የተዘረዘሩትን የወጪ ምርቶች ብቻ ነው።

2/ የጠረፍ ነጋዴ ከደቡብ ሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት የሚችለው በዚህ መመሪያ አባሪ-2 የተዘረዘሩትን የገቢ ምርቶች ብቻ ነው።

3/ የጠረፍ ነጋዴ በአንድ ወር ውስጥ የሚያስወጣው እና የሚያስገባው የምርት መጠን ግምት ከብር 40,000 /አርባ ሺህ/ ወይም ተመጣጣኝ የደቡብ ሱዳን ፓውንድ መብለጥ የለበትም።

4/ የጠረፍ ነጋዴ የሚነግደው ምርት መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተጠቀሰው ግምት እስካልበለጠ ድረስ በወር ሁለት ጉዞዎችን ሊያደርግ ይችላል።

5/ የጠረፍ ነጋዴ የሚነግደውን የምርት ዓይነት፣ መጠን እና ብዛት በድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ሰራተኞች በሚያቀርቡለት ዴክላራሲዮን ላይ መሙላት፣ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማቅረብ እና በሕግ መሠረት የሚጠየቁ የአገልግሎት ክፍያዎችን እና ታክሶችን መክፈል አለበት።

### 6. የወጪና የገቢ ምርቶች ዋጋ

1/ የወጪ ምርቶች የመሸጫ የዋጋ ግምት የሚሰላው ሚኒስቴሩ ወይም እርሱ የሚወክለው የክልል መስተዳድር በሚያወጡት ወቅታዊ የምርቶች የዋጋ ዝርዝር መሰረት ይሆናል።

2/ የገቢ ምርቶች ዋጋ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሠረት የሚወሰን ይሆናል።

## 7. በድንበር በሮች ስለሚሰጡ አገልግሎቶች

1/ የጠረፍ ነጋዴ የጠረፍ ንግድ ምርቶችን ማስወጣትና ማስገባት የሚችለው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎት በሚሰጥባቸው የድንበር በሮች በኩል ብቻ ነው፡፡

2/ በድንበር በር ለጠረፍ ነጋዴ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር አፈጻጸም የጉምሩክ ኮሚሽን በሚዘረጋው የአሠራር ሥርዓት መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 8. የመረጃ ልውውጥ

1/ ሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ ውክልና የተሰጠው የክልል መስተዳድር በአባሪ-1 የተዘረዘሩትን ወጪ ምርቶች ወቅታዊ የመሸጫ ዋጋ ዝርዝር እንዲሁም የተሰጡ እና የተሰረዙ የጠረፍ ንግድ ፈቃዶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለድንበር በር የጉምሩክ ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ያሳውቃል፡፡

2/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሚኒስቴሩ እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን  የጠረፍ ንግድ የወጪና ገቢ ዕቃዎች ስታትስቲካዊ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፡፡

## 9. የጠረፍ ንግድ ፈቃድ አጠቃቀም

የጠረፍ ነጋዴ ፈቃዱን በውሰት ወይም በሌላ መንገድ ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ወይም የሌላ ሰው የጠረፍ ንግድ ፈቃድን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 10.<u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

1/ በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ የጠረፍ ንግድ ምዝገባ፣ የጠረፍ ንግድ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት፣ ምትክ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ፈቃድ ማገድና መሰረዝ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉት ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

(ሀ) የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 35፤

(ለ) የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ደንብ ቁጥር 392/2009 (እንደተሻሻለው) ከአንቀጽ 42 እስከ 47፤ እና

(ሐ) የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና ድህረ ፈቃድ ኢንስፔክሽን መመሪያ ቁጥር 935/2015 ከአንቀጽ 33 እስከ 38፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የነዚህን ሕጎች ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

### 11.<u>አባሪዎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙት የወጪ እና የገቢ ምርቶችን የሚዘረዝሩት አባሪ-1 እና አባሪ-2 የዚህ መመሪያ አካል ናቸው፡፡

### 12.. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድረ ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥር 27 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ገብረ መስቀል ጫላ ሞጣሎ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**

አባሪ 1፦ <u>ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ሱዳን የሚወጡ ምርቶች ዝርዝር</u>

1. ፍራፍሬዎች፤
2. የተፈጥሮ ማር፤
3. በቆሎ፤
4. ነጭ ሽንኩርት፤
5. ድንች፤
6. ሻይ ቅጠል፤
7. ካናቫስ፤
8. የሻይ ቅመም፤
9. የእርሻ መሳሪያዎች /የሀገር ውስጥ/፤
10. የውበት ማስጌጫ/ቅባቶች/፤
11. ኬንኬስ/ወይካ፤
12. ቆጭቆጫ/አሸቴ እና
13. ጋንጉልሽ ናቸው።

አባሪ 2፦ <u>ከደቡብ ሱዳን ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ምርቶች ዝርዝር</u>

1. ፍራፍሬዎች፤
2. የሴቶች መከናነቢያ/Lady tobs/፤
3. ተምር/Palm nuts/፤
4. የደረቀ ተምር/Dry nuts/፤
5. የድንጋይ ወፍጮ፤
6. የእርሻ መሳሪያዎች /የሀገርውስጥ/፤
7. ቀይ ሽንኩርት፤
8. የፕላስቲክ ውጤቶች፤
9. ማንቆርቆሪያ፤
10. የወጥ ቤት ዕቃዎች፤
11. ሳሙና፤
12. ቁርጥራጭ ብረቶች፤
13. የውበት ማስጌጫ/ሂና፣
14. ሽቶ፤
15. ዕጣን፤
16. ባትሪ ድንጋይና የባትሪ ቀፎ እና
17. ባህላዊ አልባሳት ናቸው፡፡